# አትሰቀል!

(አሥራደው ከፈረንሳይ)

በገባለት ቃሉ: አባትህ ለ'ኛ አባት፤
አንተ ለኛ ሞተህ: ልንድን ከሃጢያት፤
እኛን አድናለሁ: ብለህ ከመከራ፤
መስቀል ተሸክመህ: አትውጣ ተራራ::
በጨካኞች ጅራፍ: አይገረፍ ጀርባህ፤
ምስማር አይቸንከር: በጅና በግሮችህ፤
በጦር አይወጋ: አይበሳ ጎንህ፤
አትጠጣ ፍጹም: የሃሞት መራራ፤
አድናለሁ ብለህ: እኛን ከመከራ፤
መከራህ አይብዛ: መከራችን ላይቀር፤
ተንገላተህ አትሙት: አትሰቀል! ይቅር::

ተከባብሮ መኖር: አብሮ መብላት ቀርቶ፤
ጥላቻ፤ ጭካኔ፤ መከራ በርክቶ፤
ወንድማማችነት፤ ፍቅር መተባበር፤
አንድነት፤ ነፃነት፤ ፍጹም ጠፍተው ካገር፤
መቻቻል፤ ደግነት፤ ከሃገር ተሰደው፤
ግፍ በደል በርክቶ: ሞልቶ ፈሶ ጽዋው፤
ሰው ሆነን ሰው ካልሆን: ተፈጥረን ባምሳልህ፤
ከሰማየ ሰማይ: ወርደህ ከዙፋንህ ፤
አፈር ለባሽ ገላ: ከንቱ ሥጋ ለብሰህ፤
አትሰቀል በቃ! እኛን ላድን ብለህ ::

ይልቅስ ከሰሙህ እንዲህ ምከራቸው.........!
እንደዚህ በላቸው.... !

ስልጣን ተገን አርጎ: ቀምቶ የበላ፤
ለሥጋው አድልቶ: ወገኑን ያጉላላ፤
ወንድሙን የገፋ: በደልን የዘራ፤
የሚያበዛ ት'ቢት: ሰው የሚያስፈራራ፤
ጥላቻን አንግሶ: ፍቅርን ያኮሰሰ፤
ዘረኝነት አርሶ: ቂም የነሰነሰ፤
ውሸት ያመረተ: በደል የከመረ፤
በግፍ የገደለ: ወህኒ ቤት ያጎረ፤
ቁጣዬን አብዝቶ: መከራውን ያጭዳል፤
ሕዝቤን አታጉላሉ: ከንግዲህ ይበቃል !
ብለህ ንገራቸው.........!
ስልጣን ላዋሰካቸው......... !
ልቦና ቢገዙ.... ድንገት ቢመለሱ.... ወደ ሕሊናቸው ::

*ግን፤*

*የሕዝብህን ጩኸት: እየሰማ ጆሮህ፤*
*ሰቃይ መከራውን: እያየኸው ባ’ይንህ*
*ሲካድ ሰብዕናው: ፈጥረኸው ባምሳልህ፤*
*ዝምታህ ከበዛ: ከዘገየ ፍርድህ፤*
*ላማ ሰበቅታኒ: ኤሎሄ ! ኤሎሄ ! ላ’ባትህ ልናገር፤*
*ቁም ሰቅልህ ይብቃ! እኛ አልዳንምና: አትሰቀል ይቅር!!*

*ሚያዝያ 4 ቀን 2004 ዓ.ም. (April 12/2012)*

*በስደት ለሚጉሳሉ፤ ለተገፉ ሕዝቦችና፤ ለተጨቆኑ ነብሶች ነፃነት፤ ማስታወሻ የተቋጨች::*